It is believed that this program will continue as one of MU-LSSA's projects in a more structured way cooperating with other organs in the justice system. This is due to the significance of this program to the different moot court competitions of the law school and to the legal aid center of the university. Not only that the nature of the field (law) by itself demands this kind of practical program; especially the fact that it is not such a complex and costly program to prepared, and the fact that it is a continuous program and it participates almost all law students are among the unique features of the program.

The moot court competition

The moot court competition held in MU-law school moot court hall was organized by the MU- Environmental and Natural Resources Law Center and MU- Legal Aid Center on the theme "enforcement of environmental laws in Ethiopia". This competition includes both the writing and oral. The oral competition was held between 6 groups on June 15, 2019. The competition among the finalists was held on June 23, 2019.







#ኧረ በህግ!!!

By Biruk Eshete

የሰብአዊ መብት አላማ እና ስጋቶች

የሰብአዊ መብት / human right/ መሠረቱ የጠነከረው ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኃላ ሲሆን የዓለም መንግስታት ዳግም ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ፣ ዐለም አቀፍ ሠላምን ለማስፈን እና ግጭቶችን ለመቀነስ ዋነኛ አላማቸው አድርገው ካቋቋሙት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጋር ልዩ ግንኙነት አለው።

በአሁኑ ጊዜ የሰብአዊ መብት መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳቦች(elements of human right) የምንላቸውን፡ የመናገር መብት፣ የእምነት ነፃነት ፣ የመኖር መብት እና የመሳሰሉት በብዙ ሀገሮች ህግጋት ውስጥ መካተት የጀመሩት የአሜሪካው ፕሬዚደንት ፍራንክሊን ዴላኖ ሩዝቬልት በ1941 ያደረገውን ንግግር መሠረት በማድረግ ነበር።

ለሰብአዊ መብቶች መከበርም በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ1945 እና በ1948 የወጣው የተባበሩት መንግስታት ቻርተር እና Universal declaration of human right ትልቁን ድርሻ የሚወስዱ ናቸው። ለአብነትም ያህል UNIVERSAL DECLARATION OF HUMAN RIGHT በግልፅ በ መግቢያው ላይ የሰብአዊ መብት አስፈላጊነትን እንዳተተው፡

"Disregard and contempt for human rights have resulted in barbarous acts which have outraged the conscience of mankind, and the advent of a world in which human beings shall enjoy freedom of speech and belief and freedom from fear and want has been proclaimed as the highest aspiration of the common people... All human beings are born free and equal in dignity and rights."

በተባበሩት መንግስታት ለሰብአዊ መብት ዙሪያ በዋነኛነት እና በተቀዳሚነት ከሚጠቀሰው የሰብአዊ መብት አዋጅ (human right Declaration) በተጨማሪም ከሀያ በላይ የሚሆኑ ሰብአዊ መብት ላይ የሚያጠነጥኑ ስምምነቶችን አፅድቋል ከነዚህም ውስጥ በፈረንጆቹ 1951 በስደተኞች ሁኔታ ላይ ያተኮረው ስምምነት፣ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን የፆታ ጥቃት እና ዕድሎ ለመቀነስ በ1979 የተደረገው ስምምነት እና በህፃናት መብት ጥበቃ ላይ በ1989 የተደረገው ስምምነት በዋነኝነት ተጠቃሽ የሚሆኑ አለም አቀፍ ስምምነቶች ናቸው።

በአህጉራት ደረጃም ሀገራት ሰብአዊ መብቶች እንዳይጣሱ ስምምነቶች በማዕረግ ለሰብአዊ መብት መከበር ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል ከነዚህም ውስጥ እንደ ምሳሌ የሚጠቀሰው በ1981 የተደረገው የሰብአዊ መብት ቻርተር ስምምነት ይህንን የሚያሳይ ነው።

በህዝባዊ አስተዳደር የተቃኘ መንግስት ያላቸው አብዛኞቹ ሀገራትም ይሄንኑ መነሻ በማረግ ሰብአዊ መብቶችን ከ ህገ መንግስታቸው ጋር በማጣጣም እየተጠቀሙበት ይገኛል። ለምሳሌ መንግስታት መሠረታዊ የሆኑትን ሰብአዊ መብቶች ህጋቸው ውስጥ እንደሚያካትቱ እንዲሁም ሰብአዊ መብትን የሚጋፉ ህጎችን እንደሚያስወግዱ የመከሩበት የ 1993ቱ የቬና አለም አቀፍ ኮንፈረንስ በዋነኛነት ተጠቃሽ ነው። ይህም የሰብአዊ መብት ዓለም ዓቀፊነትን የሚያሳይ ነው ።

("The principle of universality of human rights is the cornerstone of international human rights law.")

በምንኖርበት ዓለም ላይ የተደረጉ ጥናቶችም እንደሚያመሏክቱት 80% የሚሆኑ የዓለም መንግስታት ቢያንስ በአማካይ አራት እና ከዛ በላይ የሆኑ ዋና ዋና

የሰብአዊ መብት ስምምነት ላይ ፊርማቸውን አኑረዋል። ከዚህም እንደምንረዳው አሁን ላይ ሁሉም ሀገራት ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ሰብአዊ መብትን ያካተተ ህግ ያረቃሉ ፣ ይፀድቃሉ። የዓለም መንግስታት በየሀገራቸው እነዚን ሕጋቶች ቢያካትቱም መሬት ላይ ያለው እውነታ ግን በተቃራኒው ሁኖ ይስተዋላል፡፡ ለዚህም ማሳያ የሀገራት እርስ በእርስ ጦርነቶች ፣ ሽብርተኝነት ፣ የፆታ ጥቃት ወዘተ የእለት ተእለት ተግባሮች እንደሆኑ ይታያል ። የሰብአዊ መብት ከሚጣሱባቸው ሀገራት መካከል በቀዳሚነት ተጠቃሽ ከሆኑት እንደ ሶሪያ ፣ ሶማሊያ ፣ ሊቢያ ፣ ኩባእና ሌሎችም ዲሞክራቲክ የሚባሉ ሀገራትም ይህ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንደችግር ሆኖ ቀጥሎዋል ። መንግስታትም ግልፅኝነትና ተጠያቂነት ችላ በማለት የሰብአዊ መብት መርሆችን በመጣስና ለሰብአዊ መብት መከበር ክለላ ባለመስጠት የህዝቦቻቸውን ህይወት አደጋ ላይ ሲጥሉ ይስተዋላል። እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ2015 (human right watch) የሰብአዊ መብት ጥበቃ ላይ በሀገራት ደረጃ በተደረገው ጥናት እና በአሜሪካ (state department) የሰብአዊ መብት ጥበቃ ላይ በ2017 በተሰራው ጥናት እንደሚያመላክተው በ2011 በጀመረው የእርስ በእርስ እየታመሰች ያለችው ሶርያ ፣ ከ670,000 በላይ ህዝቦችዋ የተፈናቀሉባት ቡሩማ ፣ በአምባገነን መንግስት እየተመራች ያለችው ሰሜን ኮሪያ ፣ ሀሳብን በነፃ መግለፅ ወንጀል የሆነባት ኢራን ፣ የአሸባሪ ቡድን የሆነው ቦኮሀራም እየፈነጨባት ያለችው ናይጄሪያ የሰብአዊ መብት ረገጣ በብዛት የሚስተዋልባቸው ሀገራት ሆነው ተገኝተዋል። አብዛኛውን ጥናቱ ላይ የገቡ ሀገራትም የሰብአዊ መብትን በየህጎቻቸው ያካተቱና የተለያዩ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን የፈረሙ ናቸው ይሁን እንጂ ወረቀት ላይ ከማስፈር የዘለለ ትግበራ ላይ የዋለ የሰብአዊ መብት ጥበቃ እና ክለላ እያደረጉ አይደለም። እነዚህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከግዜ ወደ ግዜ እየተባባሱ መምጣታቸው የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ለማስከበር እንደ አላማ አድርጎ የተነሳውን ሰላምን በአለም ሀገራት ማስፈን አደጋ ውስጥ ከመክተቱም በላይ የሰውን ልጅ የመኖር መብት ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ ናቸው። እነዚህ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶች በጊዜ ሀይ ባይ ካላገኙ አደጋው ለትውልድ የሚተርፍ መሆኑ አይቀሬ ነው።

"There can be no peace without development, no development without peace, and neither without respect for human rights."

Human right fundamentals: A Short history of human right; David shiman, part I, copy right info: university of Minnesota Human right resource center, hrlibrary.umn.edu





#THE TALK

Dear readers in this edition under the talk we present you D.R MEHARI REDAI one of the drafter of the revised family code and associate professor school of law, Addis Ababa university.

from the previous unpublished edition

The DIGEST: - በመጀመርያ ጊዜዎን ሰውተው ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ በመፅሔታችን አንባቢያን ስም ለማመስገን እወዳለሁ:: እስኪ ስለ ሕይወቶ ትንሽ እናውራ

ዶ/ር መሃሪ:-የተወለድኩት በትግራይ ክፈለ ሃገር በያኔው እንደርታ አውራጃ ከመቐለ በስተደቡብ 50 ኪ.ሜ ርቃ ከምትገኝው ማይ ነብሪ በምትባል ገጠር ቀመስ ቀበሌ ነው:: ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ እዚያ ነው የተማርኩት:: ስድስተኛ ክፍል ስደርስ ያን ጊዜ ጀነራል የሚባል የመልቀቂያ ፈተና መውሰድ ስነ ነበረብኝ የአውራጃው ት/ት ፅ/ቤት መማርያ ክፍሎች መማርያ ክፍሎቹ ከስታንዳርድ በታች ናቸው ስላሉዋቸው ዓዲ ጉዶም ሄደን እንድንፈተን ተደረገ:: ስድስተኛ ክፍልም በጥሩ ውጤት አለፍኩኝ:: እዛ ከዚህ በላይ ትምህርት ስላል ነበረ ሰባተኛና ስምንተኛ ለመማር ኩሓ ሄድኩኝ:: እዛ ትምህርት ቤት ላይ አንደኛ ሴሚስቴሩ አጋማሽ ወደ ስምንተኛ ክፍል የሚያልፍበት አሰራር ስለነበረ ከ7ኛ ሀ አንደኛ በመውጣቴ በሁለተኛው ሴሚስተር ስምንተኛ ክፍል አለፍኩኝ:: 7ኛ እና 8ኛ በአንድ አመት ጨርሼ ዘጠነኛ እና አስረኛ በመቐለ ተማርኩኝ:: 11ኛ ና 12ኛ አስመራ ከጨረስኩኝ በሃላ ወደ አዲስ አበባ ሕግ ት/ት ቤት ተቀላቀልኩኝ::

The DIGEST: - የዩኒቨርሲቲ ሂወት እንዴት አገኙት? ሕግስ ፈልገው ነበር የገቡት?

ዶ/ር መሃሪ:-ያው እንግዲህ አስመራ እየተማርኩ እያለሁኝ እዛም ዩኒቨርሲቲ ስለ ነበር እዛው ለመቀጠል ነበር ሃሳቤ:: ነገር ግነ እዛ እያለሁኝ ያልተከፈለ ዕዳ የሚል የሕግ ጉዳዬች የሚነካካ የቴሌቪዥን ድራማ ስከታተል በጣም ይመስጠኝ ስለነበር ሕግ ለመማር ፍላጎት አደረብኝ:: ከምን ተነስተው እንደሆኑ ባላውቅም ጓደኞቼ አንተ ሕግ

ነው መማር ያለብህ አንተ የህግ ሰው ነህ ይሉኝ ነበር። ከዛ አስመራ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሕግ በቀን መርሓ ግብር ስላልነበር እኔም በአግባቡ መማር ስለነበረብኝ አንደኛ ምርጫዬ አዲስ አበባ ነበር ና ጥሩ የማትሪክ ውጤት ስለነበረኝ ምርጫዬ ተጠብቆልኝ አዲስ አባበ ገባሁ። ያኔ ሕግ ት/ት ቤት በቀጥታ አይገባም ነበር ለአንድ ዓመት በሶሻል ሳይንስ ትማርና የፍሬሽ ማን ውጤትህ ታይቶ ነበር የሚገባው። በዚህ መሰረት ውጤቴ አሪፍ ነበር ና ምርጫዬ ተከብሮልኝ ሕግ ገብቼ አራት ዓመት ተምሬ ተመረኩ።

The DIGEST: - በጣም የሚወዱት ከኮርስ ምን ነበር?

ዶ/ር መሃሪ፡-እ..... አብዛኞቹ የሕግ ኮርሶች እውዳቸዋለሁ ነገር ግን የመጀመርያ Impression ስለሆነ ይመስለኛል Introduction to Civil law የሚባለው ወደ Civil law ኮርሶች ማሸጋገርያ ኮርስ የሕግ አተረጓጎም ስልትና የሕግ ቃላቶች (Legal Jargons) የምትማርበት ኮርስ ስለነበር በጣም እወደው ነበር። እና እሱን ኮርስ አይረሳኝም።

The DIGEST: -አሁን ያሉበት የትምህርት ደረጃ በምንድ ነው ስፔሻላይዝ ያደረጉት?

ዶ/ር መሃሪ፡-እንግዲህ3ስመረቅ ጎልድ ሜዳሊስት ነበርኩኝ። ሁለተኛ ዲግሪዬን በ International economics law በአሜሪካን ሀገር ከሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ ተቀብያለሁ። ከዛ ደግሞ ማስተማሩን ቀጥዬ በቅርቡ ከዎር ዊክ ዩኒቨርሲቲ ፒኤች ዲዬን ተቀብያለሁ። አሁን በአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ተባባሪፕሮፌሰርነኝ።ስለዚህየኢትዮጵያ፤አሜሪካና እንግሊዝ ትምህርት ነካክቻለው።

The DIGEST: -መቼ ነበር ማስተማር የጀመሩት?

ዶ/ር መሃሪ፡-የተመረኩት በ1981 ዓ.ም ነው። ዩኒቨርሲቲ የተሻለ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች በ Graduate Assistant ነት ያስቀር ነበር። ሆኖም ግን የበጀት እጥረት ስለነበረ አላስቀሩኝም። ከ1982-85 አንድ የፕሮጀክቶች ልማት ጥናት ባለስልጣን የተባለ መስሪያ ቤት ውስጥ ነበር ስሰራ የነበረው፡ ፡ ግን እዚህ ዩኒቨርሲቲም በጀትና ክፍት ቦታ ሲገኝ እንዲቀጥሩኝ ማመልከቻዬን አስገብቼ ነበር፡ ፡ ስለዚህ በ1986 ዓ.ም ማመልከቻዬን ተቀባይነት አግኝቶ የስራ ጥሪ መጣልኝ። ስጠብቀው የነበረ ነገር ስለሆነ መጣሁና በ1986ዓ.ም መጀመሪያ ሴሚስቴር ማስተማር ጀመርኩኝ። ሳስተምር Teaching Methodology ከየትም አልተማርኩም። ዝም ብዬ አስተማሪዎቻችን ሲጠቀሙበት የነበረን አካሄድ ጥሩ ነው ያልኩትን ዘይቤ ይዜ ነው የቀጠልኩት። ተማሪዎቼም ጥሩ ነው እያሉ ይሰጡኝ ነበር።

The DIGEST: -መጀመርያ የሰጡት ኮርስ ምንድን ነበር?

ዶ/ር መሃሪ፡-መጀመርሪያ የሰጠሁት ኮርስ Introduction to Civil law የሚባል ነው። እወደው ስለነበር ና ጥሩ የኢንትሮዳክቶሪ ኮርስ ነው ብዬ ስለማምን በተቀበልኩት መጠን ያህል ለማስተላለፍ ሞክሬያለሁ።

The DIGEST: -ከተማሪዎች ጋር ያሉዎትን ግንኙነትና ምናልባትም ጥሩ ቦታ ደርሰውልኛል የምትሏቸው ተማሪዎች ካሉ?

ዶ/ር መሃሪ፡- Well..... ተማሪዎች ቢጠየቁ ነበር የሚሻለው። ግን ጥሩ ነኝ ብዬ ነው የማምነው፡ ፡ ብዙ አታካሮም ገጥሞኝ አያውቅም። ያው በግሬድ የሚመጣን ቅሬታ ጉዳዩን ካስረዳሁዋቸው በሓላ ቅሬታው ብዙ ሲቀጥል አላይም። በዚህ ሃያ ምናምን ዓመት ተማሪዎቼ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኝነት የደረሱ፤ የተሳካላቸው ጠበቆችም የሆኑ አሉ፤ በመንግስት መስሪያ ቤቶች በተለያየ ሓላፊነትና አማካሪዎችም የሆኑ አሉ። በርግጥ እዚህ ላይ እንዲደርሱ የኔ ሚና ምን እንደሆን መገመት አልችልም። ምናልባት የኔ ሚና እንደ ግብአት እንጂ በራሳቸው ጥረት ነው።

The DIGEST: -ዶ/ር መሓሪ ማን ብለው ነው የሚገልፁት?

ዶ/ር መሃሪ፡-ምንም.....የሕግ ባለሞያ በኔ መንገድ የተሳካልኝ ነኝ ብዬ ነው የማምነው፡፡ ምንም እንኳ በኢኮኖሚው ብዙ ባይሳካልኝ አካዳሚካሊ መድረስ ከሚገባኝ ደርሻለሁ፡፡ ለረጅም ዓመታት አስተምሬያለሁ የተወሰኑ ነገሮችን ፅፌያለሁ፤ ትዳር መስርቼ ሁለት ልጆች አሉኝ፡፡ አንዱ ልጄ በመዓረግ በሲቭል ምህንድስና ተምርቋል፤ ሁለተኛዋ ልጄ ደግሞ በዚህ ሕግ ትምህርት ቤት ሰቃይ ከሚባሉት የሶስረተኛ ዓመት ተማሪዎች አንዷ ናት፡፡ ስለዚህ በሙያም በቤተሰብም በኑሮም አልራብም.....(ሳቅ)፡፡ ቤትም ሰርቻለሁ፤መኪናም አለኝ፤ ለሞያዬም ታማኝ ነኝ ብዬ ነው ራሴን የማስቀምጠው እንግዲህ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር.....(ሳቅ)

The DIGEST: -የሕይወት መርሄ(Role Model)? የምትሉትስ?

ዶ/ር መሃሪ፡-እንዳልኩህ ከገጠር የመጣሁ እንደመሆኔ መጠን በዛኔ የነበረኝ አመለካከት ስለ ሕግ ሰው ማሰብ አልችልም ነበር፡፡ ዝም ብሎ በህፃንነቴ ግን አስተማሪ የመሆን ፍላጎት ነበረኝ፡፡ እዚህ ከመጣሁ ወዲህ ግን ሮል ሞዴል በማስተማር፤ በቅንነትም በታማኝነትም በኩል ጫና አሳድሮብኛል የምለው አሁን በህይወት የለም፡ ፡ የቤተሰብ ሕግ ቅፅ አንድ ስፅፍም ማስታወሻ ይሁንልኝ ብዬ አስቀምጫለሁ መስፍን ገብረሂወት የሚባል የሕግ አስተማሪ፤ ሲንዬር ቴሲስ ስፅፍም አማካሪዬ የነበረ ሓላ ጓደኞሞች ሁነን ቀጥለናል ምንም እንኳ የዕውቀትና የእድሜ ልዩነት ቢኖረንም፡ ፡ በሂደትም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሁኖ ነው ሂወቱ ያጠናቀቀው፡፡ ስለዚህ እሱ ጋር ቅርበት ስለ ነበረኝ በማስተማር፤ በሃቀኝነትና ሌሎች በኩል የወሰድኳቸው ነገሮች እንዳሉ ነው የምገምተው፡፡

The DIGEST: -ከዚህ በተጨማሪ በሕይወቴ አስተዋጽኦ አድርገዋል የምትሏቸው ሰዎች ካሉ?

ዶር መሃሪ፡-አዎ ብዙ ሰዎች አስተዋፅኦ አድርገዋል፡ ፡ አንደኛ ህግ መማር አለብህ ብለው ከቅን ልቡና የመነጨ ግፊት ካደረጉልኝ ሰዎች አንድ ጓደኛዬ አለ ድረስ ደምሴ ይባላል የSocial Work ምሁር ነው፡፡ ሁለተኛ አምስት ዓመት ሙሉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ በወር ኃምሳ ኃምሳ ብር እየላከ የዩኒቨርሲቲ ሂወቴ ብዙ ሳልጨናነቅ እንድጨርስ ያደረገኝ አስመራ እያለሁ የተዋወኩት (አሁንም ጓደኛዬ ነው) ሃይለማርያም ተካልኝ የሚባል ነው፡፡ ሶስተኛ ህግ ትምህርትቤት ጨርሼ ከወጣሁ በኃላና ወደ መንግስት ስራ ስገባ ሂወቴን በዛ መስመር ለመቀጠል እያስተካከልኩ እያለሁ ይሄ የአካዳሚክ ትራክ መተው እንደሌለብኝ በተደጋጋሚ እየመከረ እና እየገፋፋ ወደዚህ አንድገባ ያደረገኝ ዶክተር መንበረፀሐይ ታደሰን ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡

The DIGEST: -የፃፏቸው መፃሕፍቶች፤ የተሸለሟቸው ሽልማቶች ና ስኬቶች ካሉ ምን ይመስላሉ?

ዶር መሃሪ፡-ያው አሁን ያለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ ሲረቀቅ ሶስት አባላት ያሉት የፍትሐ ብሔር ሕጎች አርቃቂ ኮሚቴ የሚባል ነበር(ቅድም ያልኩህን መስፍን ገብረሂወት የሚሰበሰበው እኔና እንደ የህግ ምሁር እንዲሁም አንድ የጽሁፍ ባለሞያ ያካተተ ማለት ነው) በፍትሕ ብሔር ላይ ሴቶች እኩልነት አያነሳም እየተባለ ሲተች የነበረው የፊተኛው የቤተሰብ ሕግ ከፍትሐ ብሄር ሕጎች ቅድሚያ ተሰጥቶት መሻሻል አለበት ተብሎ እዛ ስራ ውስጥ ተሳትፌያለሁ፡፡ እናም የቤተሰብ ሕጉ ላይ ማብራሪያ ፅፌያለሁ፡፡ ምክንያቱ እዛ ላይ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ኑሮኝ ሳይሆን ሕጉ ሲረቀቅ የሄደበት መንገድ በቅርብ ስለተከታተልኩት እና በወቅቱ ይሄን ነገር ሳልረሳው ከመገብኩት ለወደፉት በዚህ ዙርያ ለሚፅፉ ፅሁፎች እንደ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል በማለት ነው፡፡ አሁን ብዙ ሰዎች ይሄን የሚያነቡት ምንም ነገር በሌለበት

ስለሆነ እነደ ትልቅ ነገር ተቆጥሮ በየቦታው ሰዎች እንደሚጠቀሙበት ነው የምሰማው። በስልክና በኢሜል ጭምር። ይህ ለኔ ትልቅ ሽልማት ነው። ሌላ አሁን እየሰራሁበት ያለሁት በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ አካባቢ ነው። በLabor የሚገዛና በሲቪል ሰርቨስ የሚገዛውን ዘርፎችን ረዘም ላለ ግዜ አስተምሬያለሁ። እና በዛ አከባቢ ላይ አንድ Teaching Material ነገር Compile አድርጌያለሁ። አልፎ አልፎ በመፅሄቶች የምፅፋቸው አንቀጾች በMizan Law Review የሚወጡ አሉ፤ የሰበር ውሳኔዎችም እተቻለሁ፤ በኢትዮጵያ ሕግ መፅሔትም አቅም በፈቀደው እፅፋለሁ። ዎረወ ዊክ በነበርኩበት ጊዜም ኤሌክትሮኒክ የሆነ ዓለም ዓቀፋዊ ጆርናል አላቸው እዛም ፅፌያለሁ። ስለዚህ እዚህም እዛም እሞካክራለሁ። በጥብቅናም በአንዳንድ ኩባንያዎች ሰርቻለሁ፤ ጉዳዮችን ይዤ እሰከ ሰበር በመሄድ እቆማለሁ።

The DIGEST: -ከኛው መቐለ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት ምስረታ ጋር በተያያዘ የሚሉትን ነገር ካለ?

ዶ/ር መሃሪ፡-በመቐለ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት ሲቋቋም መጀምርያ የማቋቋሚያ ሃሳብ ያመነጨው አሜሪካዊው ረይ ዊተን (Wray Witten) ነው። አንደኛ ኢትዮጵያዊ አለመሆኑና ሁለተኛ የሕግ ምሁር አለመሆኑን የማቋቋም ፍላጎት ብቻ ነበረው እንጂ ስራው እንዴት መሄድ እንዳለበት በዘርፉ ያሉ ባለሞያዎች ማማከር ስለነበረበት በዚህ ሂደት እንድንሳተፍ ከጋበዘን ሰዎች መካከል አንዱ እኔ ነበርኩኝ። በዚህ አጋጣሚ እኔና ዶክተር አሰፋ ፍስሃ የሕግ ትምህርት ቤቱ ካሪኩለም ቀርፀነዋል። ስለዚህ ምንም እንኳ የማስተማሩ እድል ባይገጥመኝ በካሩኩለም ቀረፃ ላይ ግን ተሳትፌያለሁ።

The DIGEST: -በመጨረሻም ማስተላለፍ የምትፈልጉት መልዕክት ካለ?

ዶ/ር መሃሪ፡-እንግዲህ ሕግ ከፍትህ የተቆራኘና ከፍተኛ የሆነ የሞያ ጥንካሬ የሚጠይቅ ነው። መማር አንድ ነገር ነው።ማውቅ ደግሞ ከዛ በላይ ይሄዳል እና ዋናው ቁምነገሩ ሕጉን ማወቁ ነው። ማወቅ ከትምህርት ብቻ አይመጣም። በዋናነት በራስህ ጥረት ከተማርከው በላይ መሄድ ያስፈልጋል። ስለዚህ አሁን ባለው ሁኔት እኛ ከነበርንበት የአሁኑ ተማሪ የተሻለ ነው የሚመስለኝ። ምክንያቱ አንደኛ ዘመኑ የመረጃ ዘመን ነው። ብዙ መረጃ ከኢንተርኔትም ከተለያዩ ምንጮችም ይገኛል። ሁለተኛ Law in action ,law in Context የሚለውን ህጉ በተግባር የሚፈፀምበት ሁኔታ በተመለከተ የሰበር ውሳኔዎች በሃርድና ሶፍት ኮፒ በየጊዜው እየወጣ ነው። ስለዚህ የሰበር ውሳኔዎች የተለያዩ የህግ ዘርፍ በተግባር እንዴት እየዋሉ እንዳሉ የሚያሳይ ነው። እነዚህ አመቺ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ህጎቹ አንቀፅ በማነበብ ብቻ ሳይሆን አንቀፆቹ በክርክር ነጥረው ትርጉም ወጥተው የምናይባቸው ተደራሽ የሆኑ ሰነዶች እየመጡ ነውና የራስ ጥረት ከጨመርንበት የተሟላ የህግ ባለሞያ ለመሆን የምንችልበት ዕድል ሰፊና የተመቸ ስለሆነ ሙያውን ጠበቅ አድርጎና ጠንከር አድረጎ መያዝና ለሕግ የበላይነትና ለፍትህ መስፈን በቆራጥነት መታገል የሚያስከፍለው መስዋዕትነት ለመክፈል እየተዘጋጁም ጭምር መሆን አለበት እላለሁ።

The DIGEST: -እናመሰግናለን

ዶ/ር መሃሪ፡-እኔም አመሰግናለሁ

#HASSEN'S PERSONAL INSIGHT

የመንግስት አወቃቀር በኢፌዴሪ ህገመንግስት ለግንዛቤ እና ለማስታወስ ያህል የተዘጋጀ

ሐሰን መሐመድ

ይህ ፅሁፍ በዋናነት በኢፌድሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 45 (ምዕራፍ አራት) እስከ አንቀፅ 84 (ምዕራፍ ዘጠኝ) ላይ ተሞርኩዞ ዋና ዋና ጉዳዮችን ይዳስሳል። እንደ መነሻ ግን የመንግስት አወቃቀር በአንቀፅ 1 ላይ ተደንግጓል። ይህም ፌደራላዊ እና ዲሞክራሲያዊ አወቃቀር ነው። ፌደራላዊ ሲል ከሁለት መንግስት የተዋቀረ (ክልል እና ፌደራል) እና ሉዓላዊነት ያላቸው መሆናቸውን ያመለክታል ፣ዲሞክራሲያዊ ሲል ደግሞ ህዝብ ራሱን የማስተዳደር መብት እንዳለውና በዚህም መሠረት ሁለቱም መንግስታት በህዝብ የተመረጡ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል።

ወደ ምዕራፍ አራት ስንመለስ ፣ ከላይ እንደ ተጠቀሰው ከዘጠኝ የክልሎች እና የፌደራል መንግስት የተዋቀረ የፌደራል ስርዓት ይመሰረታል። ነገር ግን ሉዓላዊነት በአንቀፅ 8 መሰረት የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ስለሆነ በክልሎቹ ውስጥ ያሉ ብሔሮች ብሔለሰቦች እና ህዝቦች በአስፈለጋቸው ጊዜ ክልል የመመስረት መብት አላቸው። ይህ መብት ለአጀማመር እና ለአሠራር ሲባል ፌዴሬሽኑ በዘጠኝ ክልሎች ተጀመረ እንጂ በዚያው ያበቃል ማለት አይደለም። የክልልነት ጥያቄው በራሳቸው በህዝቦቹ ምክር ቤት በ2/3ኛ ድምፅ ማለፍ ብቻ ነው የሚጠበቅበት እናም የክልሉ ምክር ቤት ጥያቄውን መቀበል እና ህዝበ ውሳኔ ማዘጋጀት እንጂ አለመቀበል አይችልም። ከዚህም የምንረዳው ክልሎች (ዘጠኙ) አስተዳደርዊ አወቃቀራቸው በውስጣቸው ያሉትን ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ምክርቤት እንዲኖራቸው በሚያስችል መልኩ መሆን እንዳለበት ነው። አለበለዚያ ክልል የመሆን መብታቸው አደጋ ላይ ይወድቃል ምክንያቱም ቢፈልጉ እንኳ ምክርቤት ከሌላቸው ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም።

ከክልሎች እና ከፌደራል መንግስት የተዋቀረ ስርዕት ከተመሰረተ በኃላ በምዕራፍ አምስት ደግሞ አደረጃጀታቸውን እና ስልጣናቸውን ይወስናል። ሁለቱም መንግስታተት ሶስት መሠረታዊ ተቋመማት ይኖሯቸዋል ህግ አውጭ ፣ ስራ አስፈፃሚ (ህግ አስፈፀፃሚ) እና ህግ ተርጓሚ (የዳኝነት)። ሁለቱም በየስልጣነናቸው (በ51 እና 52 በተሰጣቸው) ከፍተኛው የስልጣን አካል የምክር ቤቶቹ (ህግ አውጭው) ነው። ይህም የሆነው በ45 መሠረት ፓርላሜንታዊ ስርዓተ መንግስት ስለሚያዝ ነው። በፓርላሜንታዊ ስርአት የህዝብ ሉዓላዊነት ተግባራዊ የሚደረገው በመረጣቸው ተወካዮቹ አማካኝነት ስለሆነ ነው። ሁለቱም መንግስታት አንዳቸው በአንዳቸው ስልጣን ጣልቃ መግባት አይችሉም ነገር ግን የፌደራሉ መንግስት ሰብአዊ መብትን እና ህገ-መንግስቱን አደጋ ላይ የሚጥል ጉዳይ ላይ ጣልቃ ሊገባ ይችላል።

የስልጣን ክፍፍልን በተመለከተ ብዙ ጊዜ በፌደራላዊ ስርዓት ውስጥ የፌደራል መንግስት ስልጣን የሚሆኑት አጠቃላይ የአገር ጉዳይ እና ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ክልሎችን የሚያነካኩ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህም ለምሳሌ የአገር ደህንነት ፣ የጦር ሃይል ፣ ገንዘብ ማተም ፣ የውጭ ግንኙነት ፣ የውጭ ንግድ እንዲሁም ከክልሎች መሀል ንግድ ፣ የተፈጥሮ ሀብት ወንዞች የመሳሰሉት ናቸው። የኛም ህገ-መንግስት ከዚህ የተለየ አይደለም ክልሎች በመርህ ደረጃ ለፌደራሉ

መንግስት ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ያሉ ወይም በግልፅ በ51 ያልተሰጠው ጉዳይ የነሱ ስልጣን ነው። ይህም ሆኖ ሳለ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደራቸውን የተመለከቱ በግልፅ የተቀመጡ ስልጣኖች አሏቸው። ወደ ፌደራሉ መንግስት ተቋማት ስንገባ በምእራፍ ስድስት ህገ-መንግስቱ ሁለት ምክር ቤቶች እንደሚኖሩ ይደነግጋል። የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማው) እና የፌዴሬሽን ምክርቤት። ነገር ግን ከላይ እንደተጠቀሰው ከፍተኛው ስልጣን እንዲሁም ህግ አውጪነት የፓርላማው ነው። ፓርላማው በየ 5 አመት ይመረጣል። አባላቱ የሚመረጡት በአንድ የምርጫ ክልል አብላጫ ድምፅ ሲያገኙ ነው። የምርጫ ወረዳዎች የሚወሰኑት በአንቀፅ 103 መሰረት በየ10 አመቱ የህዘዝብ ቆጠራ ከተካሄደ በኋላ ለምሳሌ በቅርቡ ይፋ የሆነው የህዝብ ቆጠራ የሚያሳየው የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 80 ሚሊዮን ሲሆን (የመራጭ) የፓርላማ ወንበር ቁጥር 530 ነው (ማለት 550 ቢሆንም 20 ወንበር ለአናሳ ብሄሮች የተያዘ ነው ምክንያቱም በህዝብ ቁጥር ማነስ ምክንያት ሳይወከሉ እንዳይቀሩ ነው)። ስለዚህ አንድ የምርጫ ክልል ወደ 140 ሺ ህዝብ ይይዛል ማለት ነው። ሆኖም ይህ ቁጥር በየጊዜው በተለያዩ ምክንያቶች ስለሚቀየር የህዝብ ቆጠራ ማድረግ ወሳኝ ነው። ከዚሁም ጋርም የምርጫ ክልል ድንበሮችም ይቀየራሉ።

ምርጫውን የሚያሸንፉት በአብላጫ ድምፅ ነው ። የተላያዩ ተወዳዳሪወዎች በአንድ የምርጫ ክልል ተወዳድረው ከነሱ መሃል አብላጫ ድምፅ ያገኘው ወንበሩን ያሸንፋል ። የተቀሩት ግን የመረጣቸውን ህዝብ ወክለው ወንበር ማግኘት አይችሉም ። ስለዚህም ለምሳሌ በአገር ደረጃ አንድ ፓርቲ 60 % ድምፅ ቢያገኝ እና ሌላው ፓርቲ ደግሞ 40% ቢያገኝ ባለ 60ው አሸናፊ ሆኖ ባለ 40ው ተሸናፊ ይሆናል ። ስለዚህም ብዙዎች ይህ ስልት የውክልና ችግር አለበት ይሉታል ። ነገር ግን ጠንካራ ጎንም አለው ። በዚህ ስልት የሚመሩ አገሮች ውስጥ ፓርቲዎች እንደ አሸን አይፈሉም ። ጠንካራ ፉክክር የሚያደርጉ ጥቂት ፓርቲዎች ናቸው ብዙ ጊዜ የሚኖሩት ። ስለዚህም የመንግስት ስልጣን (በተወሰነለት ዓመት) የተረጋጋ ነው ። ሆኖም አማራጭን ይገድባል ። ለምሳሌ ዩ.ኤስ. ኤ.።

ከዚህ በተለየ ደግሞ አንዳንድ አገሮችነ የሚከተሉት ስልት በምርጫ ክልሎች ውስጥ ከተወሰነ የህዝብ ቁጥር በላይ (ብዙ ጊዜ ከ2-5 %) የተመረጠ ያንኑ ህዝብ ወክሎ ወንበር ያገኛል ። በዚህ ዓይነት ስልት የሚመሩ አገሮች ውስጥ ፓርቲዎች ይበዛሉ ። ወንበር የማግኘት ዕድላቸው ሰፊ ነው ። ስለዚህ ብዙዎች የሚሉት መንግስት መመስረት አስቸጋሪ ነው ። ብዙ ጊዜ በጣምራ ነው እሱም ግን ጊዜው ሳይደርስ ይፈርሳል ። ምሳሌ እስራኤል እና ጃፓን ነገር ግን ይህ ስልት ጠንካራ ጎንም አለው ።እኛ ከምንጠቀመው በተሻለ ለህዝብ የውክልና ዕድል ይሰጣል ። ምክንያቱም ተመራጩ መሸነፍ አለመሸነፉ ሳይሆን የተወሰነ ህዝብ ከመረጠው ይወከላል ። ሌላው ጠንካራ ጎን ለህዝብ ብዙ አማራጭ ይሰጣል ። ይህም በጣም ዲሞክራሲያዊ ያደርገዋል ። ነገር ግን ጀማሪ አገረሮች ዲሞክራሲን በዚህ ስልት እንዲጀምሩ አይመከሩም ።ምክንያቱም ልማዳቸው እስኪዳብር የተረጋጋ መንግስት ያስፈልጋቸዋል ።

ከላይ እንደተጠቀሰው እንዲህ በምርጫ ክልሎች ብቻ ሳይሆን በአገር ደረጃም አብላጫ ድምፅ ያገኘው የፖለቲካ ድርጅት ስራ ላስፈፃሚውን ይመሰርታል ። ይህም የሚሆነው ከምክርቤቱ ውስጥ ነው ምክንያቱም ስርዓቱ ፓርላሜንታዊ ስለሆነ ። ያሸነፈው ፓርቲ አንድ ሳይሆን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ (ማለት አብላጫ ድምፅ ያገኘ ፓርቲ ከሌለ) ድርጅቶቹ በስምምነት ጥምር መንግስት ይመሰርታሉ። ምክር ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥያቄ እና በምክር ቤቱ ፍቃድ ሊፈርስ ይችላል ። ነገር ግን በዚህ ጊዜ የአገሪቱ ፕሬዝዳንት እንደገና

ጥምር መንግስት እንዲመሰረት ጥሪ ያደርጋል ። በሳምንት ጊዜ ውስጥ ይህ ካልሆነ ምክር ቤቱ ፈርሶ ምርጫ ይደረጋል ።

ወደ ምክር ቤቱ ስልጣን ስንመጣ በፌደራሉ መንግስት በ51 ከተሰጠው ስልጣን የተለየ አይደለም ። ነገር ግን 55(6) ላይ ለየት ያለ ስልጣን (በ51 በግልፅ ያልተሰጠ) ተሰጥቶት እናገኛለን ። በ52 መሰረት በ51 በግልፅ ያልተሰጠ ማለት የክልል ስልጣን ነው ማለት ነው ። አንቀፅ 55 (6) የፌዴራሉ መንግስት አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሲባል በፌዴሬሽን ምክር ቤት የታመነባቸው የፍታብሔር ጉዳዮች ላይ ህግ ሊያወጣ ይችላል ። አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር የሚለው ዓላማ በህገ-መንግስቱ መግቢያ ላይ የሰፈረ ዓላማ ሲሆን ሁሉንም ክልሎች ያስተሳሰረ አንድ ገበያ እንዲኖር ለማድረግ የታሰበ ነው ። ግን ይህን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ መንግስታት የሚሰጣቸው ስልጣን የንግድ ህግ ማውጣት እና በክልሎች መሃል የሚካሄድ ንግድን መቆጣጠር ናቸው ። በኛም ህገ መንግስት ይህ ስልጣን ለፌዴራል መንግስት ተሰጥቷል ። ከሌሎች ፌዴሬሽኖች በተለየ ግን የኛ ፌዴራል መንግስት የክልል ስልጣን በሆኑት የፍታብሔር ጉዳዮች ላይ ህግ የማውጣት ስልጣን ሊኖረው ይችላል ። ይህ ደግሞ ከሌሎች ፌዴሬሽኖች በላይ ጠንካራ አና ብዙ ገቢ ያለው ፌዴራል መንግስት እንዲፈጠር ያደርጋል ። የንግድ ህግ የማውጣት ስልጣን ብቻውን ጠንካራ እና ሃብታም ፌዴራል መንግስት እንደሚፈጥር በታሪክ በሌሎች ፌዴሬሽኖች ታይቷል ። ምሳሌ ዩ.ኤስ.ኤ እና አውስትራሊያ ። የኛ ደግሞ ከነሱ በላይ ነው ። ስለዚም ፌዴራል መንግስት ላይ በጣም ጥገኛ የሆኑ ክልሎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል ።

ሌላው ሁለተኛው ምክር ቤት(የፌዴሬሽን ምክር ቤት) ምንም አይነት የህግ የማውጣት ስልጣን የሌለው በሌሎች ፌዴሬሽኖች ያልተለመደ ልዩ ተቋም ነው ። ይህ ምክር ቤት በዋናነት የዳኝነት ስልጣን (ህገ መንግስቱን የመተርጎም ወይም ህገ መንግስታዊ ክርክሮች ሲነሱ ውሳኔ መስጠት(62 እና 83) ሲሆን ከዚህም ባሻገር ከክልሎች ጋር የተያያዙ ስልጣኖችም አሉት ። ለምሳሌ አለመግባባት ሲኖር ፣ የጋራ ገቢዎችን እና ድጎማዎችን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል ። ይህ ምክር ቤት ከሌሎች ፌዴሬሽኖች ልዩ ነው የተባለበት ምክንያት ሁለት ናቸው ።

1ኛ. ፌዴሬሽኖች ባለ ጣምራ ምክር ቤት ናቸው። አንደኛው የመላ አገሪቱ ተወካይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በፌዴራሉ መንግስት ውስጥ የክልሎች ተወካይ ነው ። ሁለቱን ግን የህግ አውጭነት ስልጣን አላቸው ። ይህም ስልጣን የተወሰነውን በተናጠል ሌላውን ደግሞ በጋራ ይሰሩበታል ። የኛ ፌደሬሽን ምክር ቤት ምንም እንኳ በስም ምክር ቤት ቢባልም ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት ሃላፊነት የለውም ። ምንም ዓይነት የህግ አውጭነት ስልጣን አልተሰጠውም ። ይህ ስልጣን ሙሉ በሙሉ የተወካዮች ምክር ቤት ነው ። ከላይ እንደተጠቀሰው የምክር ቤቱ ዋነኛ ስልጣን የዳኝነት ነው ። ይህም ወደ ሁለተኛው ነጥብ ይወስደናል ።

2ኛ. የዳኝነት ስልጣን (በተለይም ህገ መንግስት የመተርጎም ስልጣን በብዙ አገሮች የፍርድቤቶች ነው ። ይህም ወይ በመደበኛ ፍርድ ቤቶች አሊያም በልዩ ህገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት የሚከናወን ነው ። ይህም የሆነው ፍርድ ቤት ከፖለቲካዊ ተቋማት (የህዝብ ተመራጮች) ገለልተኛ እና ተፃራሪ ሁኖ የሃይል ሚዛን ተጠብቆ ሁሉም ተቋማት ለህግ ተገዥ እንዲሆኑ እንዲሁም የግለሰቦች መብት በድምፅ ብልጫ እንዳይገፈፍ ያደርጋል ። ወደኛ ህገ መንግስት ስንመጣ ይህ ህገ መንግስት የመተርጎም ስልጣን ከፍርድ ቤት ይልቅ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው የተሰጠው ። አርቃቂዎቹ እንዳብራሩት ምክንየቱ ምክር ቤቱ የብሔር በሔረሰቦች እና ህዝቦች ተወካይ ስለሆነ ነው። ህገ መንግስቱ ከመግቢያው እንደምንረዳው የብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ስምምነት ውጤት

ነው ። በተጨማሪም በአንቀፅ 8 እንደተደነገገው ሉአላዊነት የብሄር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ነው። ስለዚህ ይህ ስምምነት በራሳቸው በህዝቦቹ ተወካዮች ነው መተርጎም ያለበት እንጂ ለሌላ ለማይወክላቸው አካል አሳልፎ መስጠት ኣይገባም ። ስለዚህም ይህ ስልጣን ምክር ቤቱን ከሌሎች ፌዴሬሽኖች ልዩ ያደርገዋል ።

የምክር ቤቱ አባላት የሚመረጡት በክልል ምክርቤቶች ወይም በቀጥታ በህዝብ ነው ። እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ እና ህዝብ ቢያንስ ኣንድ ተወካይ ኖሮት ከዛ ባለፈ ለኣንድ ሚሊዮን ህዝብ ኣንድ ተወካይ ይኖረዋል ። እዚህ ላይ ኣንድ ሚሊዮን የሚለው በእያንዳንዱ ብሔር ብሔረ ሰብ እንጂ ከክልሉ ጠቅላላ ህዝብ ኣይደለም ።

በምዕራፍ ሰባት መሰረት የአገሪቱ ርእሰ ብሄር (ፕሬዝዳንት) የሚመረጠው በሁለቱ ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ ላይ በሁለት ሶስተኛ ድምፅ ነው ። ነገር ግን ተመራጭ ዕጩው የግድ የምክር ቤት አባል መሆን የለበትም ። አንቀፅ 70 (1) እጩ የማቅረብ ስልጣን የተወካዮች ምክር ቤት ነው ሲል ከየት እንደሚሆን ምንም አላለም ። 70 (3) ደግሞ የምክር ቤት አባል ከሆነ የተመረጠው ወንበሩን ይለቃል ይላል ፤ይህ ማለት ከምክር ቤቱ ውጭ እጩ ሊቀርብ ይችላል ። ዋናው ነገር እጩ አቅራቢው ፓርላማው ሲሆን የግድ ከምክር ቤቱ ነው የሚል እንድምታ ግን የለውም ። ፕሬዝዳንቱ የመንግስት መሪ ሳይሆን የአገሪቱ ርእሰ ብሄር ስለሆነ በዋናነት የአገሪቱ ገፅታ ወይም ምልክት እንዲሆን ነው የተፈለገው ። እናም ከዚያው ጋር የተያያዙ ስልጣኖች ናቸው የተሰጡት ።

ለምሳሌም ሀገሪቱን የሚወክሉ ሰዎችን መሾም እነዲሁም ከውጭ የሚመጡትን መቀበል ፣ ሽልማቶችን እና ወታደራዊ (ከፍተኛ) ማዕርጎችን መስጠት ናቸው ። ምንም እንኳን ጠቅላይ ሚኒስትሩ የጦር ሀይሎች ጠቅላይ ኣዛዥ ቢሆንም የጦር ሀይሉን ከፍተኛ ማዕረግ ሀገርን ወክሎ ፕረዝዳንቱ ይሰጣል ። ከዚህ በተጨማሪም በህግ መሰረት ወንጀለኛ ተብለው ለተፈረደባቸው ይቅርታ ያደርጋል ። በአንቀፅ28 (2) መሰረት በሰው ልጅ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ፈፅመው የሞት ፍርድ ለተፈረደባቸው ቅጣቱን ወደ ዕድሜ ልክ ሊያሻሽል ይችላል ።

የአገሪቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እና የሚንስትሮች ምክር ቤት ናቸው (ምዕራፍ ስምንት) ስራ አስፈፃሚው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲመራ እሱም ከፓርላማው ይመረጣል ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሚኒስትሮቹን (ካቢኔውን) ከምክር ቤት ኣባላት ወይም ከዛ ውጭ መልምሎ በፓርላማው ያፀድቃል ። የስራ አስፈፃሚው ስልጣን ከምክር ቤቱ ስልጣን የተቀዳ የሆነና ነገር ግን በአጠቃላይ ማስፈፀም (ስሙ እንደሚያመለክተው) እና መተግበር ላይ ያተኮረ ነው ። በዋናነት ስልጣን የፓርላማው ሆኖ የሱን ውሳኔ እና ህግ ያስፈፅማል ማለት ነው ። ለዚም ምክንያቱ የመንግስት ስርዓቱ ፓርላሜንታዊ ስለሆነ ነው ። ፓርላሜንታዊ ማለት የህዝብ ተወካዮች የመጨረሻው ስልጣን ባለቤት የሆኑበት እና ሌሎች ፣ በተለይ ስራ አስፈፃሚው ከውሳኔ ተቋቁሞ ሃላፊነቱን ለራሱ ለፓርላማው ይሆናል ። የጎንዮሽ የስልጣን ክፍፍል (በሶስቱ መሰረታዊ የመንግስት ኣካላት መካከል) በፓርላሜንታዊ ስርዓት ውስጥ ብትንሹ ነው ተግባራዊ የሚሆነው ። ይህ የስልጣን ክፍፍል (የጎንዮሽ) በሶስት መልክ ይካሄዳል ፤ ተቋማዊ ፣ በሰው ሃይል እና በስልጣን ። ብዙ ጊዜ የፕሬዝዳንታዊ ስርዓት (ዩ.ኤስ.ኤ) ውስጥ ይህ ክፍፍል በምሉ ተግባራዊ ሆኖ የርስ በርስ ቁጥጥርን እና የሃል ሚዛን እንዲኖር ያደርጋል ። ተቋማዊ ማለት ሶስቱም ተቋማት የተለያዩ መሆን ኣለባቸው ማለት ሲሆን በሰው ሃይል ደግሞ የአንዱ አባል የሌላው አባል ሊሆን አይችልም። በስልጣን እያንዳንዱ አካል ተለይተው የሚሰጡት ሃላፊነቶች ይኖሩታል ። ከአንደኛው ስልጣን የተቀዳ

ስልጣን(እንደ ፓርላሜንታዊ ስርዓት) ሳይሆን እያንዳንዱ የራሱ የስልጣን ግዛት ይኖረዋል ። ለምሳሌ በዩ.ኤስ.ኤ ፓላማው ገንዘብን በተመለከተ ሙሉ ስልጣን ሲኖረው ፤ ፕሬዝዳንቱ ደግሞ በጦርነት አና በውጭ ጉዳይ ላይ ባለ ሙሉ ስልጣን አለው ። እናም ኣንዱ በሌላው ስልጣን ላይ ጣልቃ መግባት አይችልም እንዲሁም መወሰን አይችልም ። ህግ መተርጎምንም በተመለከተ ከአገሪቱ የበላይ ህግ(ህገ መንግስት) ጀምሮ ማንኛውም ህግ የመተርጎም እና በነሱም ላይ የሚነሳ ክርክር ላይ የመወሰን ስልጣን የፍርድ ቤቶች ነው ። በፓርላሜታዊው ስርዓት ግን ዋናው የመወሰን ስልጣን(በሁሉም ጉዳይ ላይ) የህዝብ ተወካዮች ሆኖ መተግበር ግን ለስራ አስፈፃሚው ይሰጣል ። ስለዚህም በስራ አስፈፃሚው እና በፓርላማው መካከል ብዙም የጎንዮሽ የስልጣን ክፍፍለ የለም ማለት ይቻላል ። ተቋማዊ ብቻ ነው ልዩነቱ እንጂ በሰው ሃይልም ቢሆን በአብዛኛ ስራ አስፈፃሚው ከፓርላማው ነው የሚቋቋመው ። የኛም ስርዓት ከዚህ የተለየ አይደለም ። ከአንድ ጉዳይ በስተቀር። ልክ እንደ ፕረዝዳንታዊ ስርዓት አንቀፅ 77(8) የውጭ ጉደይ ፖለሲን የማውጣት ስልጣን የስራ አስፈፃሚው (ሚኒስትሮች ምክር ቤት) ነው ይላል ። ፓርላማው ይህንን የተመለከተ ስልጣን በአንቀፅ 55 አልተሰጠውም ። ይህ ለየት ያለ ጉዳይ ነው ። በተቀረ ግን ፓርላሜናታዊ ስርዓትን የተከተለ ህገ መንግስት ነው ። የዳኝነት አካላትን በተመለከተ በሁለቱም ስርዓቶች ብዙም ልዩነት የለም ። ተቋማዊ የሰው ሃይል እና የስልጣን ክፍፍል አለው ። ነገር ግን ህገ መንግስትን በተመለከተ የተለየ አቋም እንዳለው የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ስልጣንን በዳሰሰንበት ክፍል አይተነዋል ። ያም ሆኖ በአንቀፅ 78 ህገ መንግስቱ ነፃ የዳኝነት አካል ያቋቋመ ቢሆንም ብዙ ባለ ሙያዎች ይህ ዋስትና የሌለው ነፃነት ነው ይላሉ ። ህገ መንግስት የመተርጎም ስልጣን የፍርድ ቤቶች ካልሆነ ዳኞች ራሳቸውን ከሌሎች የመንግስት አካላት የመከላከል አቅም የላቸውም በሚል ማለት ነው ። የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች እና በህግ በተቋቋሙ የፍትህ አካላት ብቻ ይሆናል። ከመደበኛ ፍርድቤቶች ውጭ የሚቋቋሙ የዳኝነት አካላት ሊኖሩ ይችላሉ ማለት ነው ፤ ለምሳሌ በአስተዳደር ህግ ውስጥ እንደተጠቀሰው ዓይነት የዳኝነት አካል ሊኖር ይችላል ። ሌላው ራሱ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በዋናነት የዳኝነት ስልጣን ነው ያለው ፤ በህገ መንግስት ጉዳይ ማለት ነው። በተጨማሪም ጋብቻ እና የመሳሰሉት ጉዳዮችን በተመለከተ በአንቀፅ 34(5) እና 78 (5) መሰረት የኃይማኖት ወይም የባህል ፍርድ ቤቶች ሊቋቋሙ ይችላሉ ፤ በስራ ላይ ያሉትም በህገ መንግስቱ እውቅና ተሰጥቷቸዋል ። ከነዚህ ውጭ ልዩ ፍርድ ቤቶች አይቋቋሙም ። እነዚህም ቢሆኑ ስራቸውን በህግ ብቻ ይሰራሉ ። ከዚህም ሌላ መደበኛ የስነ ስርዓት ህጎችን ብቻ ነው የሚከተሉት እንጂ የተለየ ስነ ስርዓት ሊከተሉ አይችሉም ።

በፌዴራልም ሆነ በክልል መንግስታት ሶስት እርከን የዳኝነት አካላት ተቋቁመዋል ። በፌዴራል ጉደዮች (ህጎች) ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፤ በክልል ጉዳዮች (ህጎች) ደግሞ የክልል ፍርድቤቶች ስልጣን አላቸው ። በክልል ጉዳዮች ላይ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻው የሰበር ስልጣን አለው ። በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የመጨረሻው የሰበር ስልጣን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲሆን ለየት የሚየደርገው ግን ይህ ስልጣን በፌዴራል ጉዳዮች ብቻ ሳይወሰን በማንኛውም የህግ ስህተት ጉዳይ ላይ ተግባራዊ ይሆናል ። ስለዚህ በክልል ጉዳይም ላይም ቢሆን የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ስልጣን አለው ማለት ነው ።

#INFOTAIMENT

By Sarah Daniel

It pays to remember facts about people

Yes, fortunately, there are no two faces exactly alike. If all faces did look alike, we couldn't remember them, or the names, memory system or not. I have been challenged many times to remember the first names of a set of identical twins. So far, I have always been able to spot one difference, however minute, in their faces. It is to this difference that I would associate their names. So, as the French say, "vive la difference!"

If you have studied the previous chapters on how to remember names and faces; and if you tried the method s, you should be gently improved by now. Although in most cases it is the second, or given names to remember, some of you may be interested in remembering first or given names as well. This too, can be done with a conscious association. You can use a substitute word for the first name, and get that into your original mental picture;

It is the common wonder of all men, how among so many millions of faces there should be none alike

Sir Thomas Browne

or, you can picture someone you know very well, having the same first name, with the person you wish to remember.

Substitute words for first names are easy to find; harry could be "hairy"; Clark could be "clock"; for William, I always picture a man with a bow and arrow as William tell, while money or "rich" always means Richard to me. Anne could be "ant"; Marion could be "marrying"; for Gloria, you might see the American flag (old glory) ,etc.

If you use the substitute word idea for remembering first names, after a while you will have one at your fingertips for any one you meet.

The system of picturing a friend of yours whose first name is the same as the person whom you want to remember, might work just as well for you. If you meet a Mr. john Sitrous, you could use the word "citrus" to associate to an outstanding feature; then put your friend, john, into the picture somehow (in ridiculous way) and

you'll remember that Mr. Sitrous' first name is john.

Again, it is not for me to tell you which idea to use, you may use one or both, as the circumstances demand. This is entirely up to you. If you find that you can remember first names with one system better than another, and then by all means, use the one that helps you the most.

If at first, you have a bit of trouble remembering the first names, don't let it bother you; just use the second name. Keep at it for a while and you'll soon be able to remember first names just as well as you do second names, vice versa. You won't insult anyone by remembering only his last name. Benjamin Disraeli had an out even if he forgot his names; he once said, "when meet a man whose name I cannot remember, I give myself two minutes, then if it is a hopeless case, I always say, and how is the old complaint?" since most of us have some sort of old complaint or other, Disraeli probably flattered everyone he used this on, making then believe that he remembered them quite well. However, no need for subterfuge; use my systems and you will remember names and faces.

More important, I think, than remembering first names, is to be able to remember pertinent facts about the people you meet. This holds true for business and social life. Businesswise, particularly, since it is often helpful to remember what items or style numbers you sold to certain customer, or, if you're a doctor, to remember patients' symptoms and ailments, etc. it is also very flattering to meet a person whom you haven't seen in some time and have him ask about things that are close to you, but would ordinarily have no interest to him. This will not only make people like you (people always like you if you show an interest in their interest) but can be quite an asset in business.

The method is the same as for remembering first names. Just put the thing into your association when you're memorizing the name and faces. If I met an Mr.Beller, whom I want to impress, an d knew he was an avid stamp collector I might associate "bell" to an outstanding feature on his face, and then associate stamps to that bell.

Some of you may feel that this might confuse you into thinking that the man's name is Bellstamp; but again, true memory

tells you difference. You'll know that the name is Beller (to make sure, you could use bell-law in the original association) and you'll be able to flatter him by asking, or talking, about his stamp collection.

During my own performances, I will usually meet doctors, judges, c, mayors and many people with titles other than "mister." It is essential for me to address them correctly, because even though I remember their names, people with titles may be insulted if I do t use that title, or if I forget it. The same ideas apply; I simply put something into my original associations which will remind me of the title. Anything will do; the first object that comes to mind when you hear the title usually best. I always picture a stethoscope to remind me of "doctor" because that's the first thing with which I associate doctors. Of course, scalpel, hypodermic, operating table, or anything like that would suffice.

When I meet a judge, or always put gravel into my mental picture. This is enough to remind me to address this personas "judge" you might like to picture the juridical robe; that's just as good. Years ago, I recall seeing a picture of New yorks mayor jimmy walker, wearing a top hat. For some reason, this picture has always stuck with me. Now, whenever am Introduced to a mayor of a town at an affair, I make sure to get a top hat into my association.

I have done quite a few performances for servicemen and I have had to prepare a substitute word beforehand to remind me as whether the person was a sergeant, corporal, lieutenant, captain, major, or what have you. As I met each man, I would put this substitute word into my association of names to face, and I did address each man correctly.

So you see that any word can be put into your associations to remind you of things pertaining to the person, as well as his or her name I have mentioned time and again, the fact that you must use these ideas in order for them to work for you. I do this only because it is important enough to warrant repetition. If you maintain the attitude that nothing will help your terrible memory, then nothing will, because you won't let it. Take positive view of it all; try these ideas and you'll be pleasantly surprised.

I've always told you that these ideas and methods are merely aids to your

true memory. If you didn't have the capacity to remember to begin with, you wouldn't remember, no matter how many systems you used; nor could you remember the systems. If you were to make an extreme effort to remember, you would; there's no question about that. The problem is that were too lazy to make the effort.

Remembering the right person's name at the proper time may perhaps mean a great deal to you, sometime in the future. It might be the stepping stone to a better job, a bigger opportunity or a much better sales of contract, etc. so, try these systems, use them, and I believe you'll be well paid for your efforts



continued from page 16

and with irrational glimpse of the public, revolt and frustrate the established, norms, values, culture and whatsoever attribution that could be given to the society, on mystic ideals. Such attacks are mainly triggered by Artists of any kind and everywhere.

The work of Art, in any manner, cannot be alienated from the personality of the Artist, for it is its manifestation that might have or not a direct connection, of course. Oscar Wilde (1891) had written the following:

Blake's works were never "published" in the modern sense of the word. Instead, he published the poems himself using a process he called "illuminated printing", a method that was unique in the history of English writing.

Unlike other printing methods at the time, Blake's method made it possible not only to print both text and illustrations on the same page and in a single printing process, but also to print on both sides of a page

- Poetic Sketches; 1783
- Island in the Moon; 1784
- Songs of Innocence and of Experience: 1788
- The Book of Thel; 1790
- The Marriage of Heaven and Hell; 1793
- Songs of Experience; 1794
- Other famous works include 'Europe', 'America', 'Visions of the Daughters of Albion' and 'The Book of Urizen'

The ten golden rules of argument


Golden Rule 1: Be prepared.

Golden Rule 2: When to argue, when to walk away.

Golden Rule 3: What you say and how you say it.

Golden Rule 4: Listen and listen again.

Golden Rule 5: Excel at responding to arguments.





Golden Rule 6: Watch out for crafty tricks.

Golden Rule 7: Develop the skills for arguing in public.

Golden Rule 8: Be able to argue in writing.


Golden Rule 9: Be great at resolving deadlock.

Golden Rule 10: Maintain relationships.

EMOTIONS



We call intense feelings such as joy and fear our emotions. They seem to well up from deep inside the brain. This is because the most basic emotions are related to our primitive survival instincts. More complex emotions probably developed later in our evolutionary history. Our ability to control our emotions, and use them constructively, is sometimes described as emotional intelligence.



FEAR



When faced with dangerous situations, it is important to feel some level of fear. If you were not afraid of road traffic, for example, you might get knocked down by a car or truck. Fear triggers physical reactions that give you superpowers, so you can run away from a fierce dog and even jump over a fence to escape. However, many of the situations that frighten us in modern life do not require this type of physical response, and the fear can lead to stress-related illnesses.

Body Language

Our body postures say a lot about how we are feeling. Some are obvious, like jumping for joy or slumping in defeat. Many are harder to define and more difficult to pick up, but we can often read such body language anyway—especially when someone's expression doesn't match up. The confident body language but sad expression above gives a strange mixed message.

Acting

Actors are judged by their ability y to express emotions that they do not really feel. This can be difficult, so one performance technique, known as "the Method," involves actors becoming immersed in the thoughts and emotions of the characters they are playing. Sometimes they do this so well that they get completely carried away.

Faking it

We all try to conceal our emotions sometimes. We try not to look bored when visiting relatives or try to look happy when we are sad. Some people in public life make it their business to smile all the time. But the difference between a real smile and a fake one is obvious if you see them side by side—in a real smile, the eyes smile, too

GOOD AND BAD

HABITS

We all have habits that help us get through life. When you wash your hands do u stop to think how to get them wet, apply the soap, use it to clean your skin, and then rinse it off? Probably not. You automatically do it, because it's a habit. It's also useful, unlike bad habits such as nail biting all habits are formed by repetition, which programs your brain so that you behave like a robot and once formed, they can be very difficult to break.

Programmed

BEHAVIOR

Habits are formed by repeated pattern. These work creating nerve networks in the brain. Those work like the simple programs used in an appliance like a washing machine—once it is turned on the program runs by itself. So when you start brushing your teeth, the habit program takes over to complete the job.

photo gallary



3rd year law sudents winner's of MULSSA cup



1st year law sudents during MULSSA cup



2nd year law students during MULSSA cup



4th year law students during MULSSA cup



3rd year law students celebrating half life



5th year law students

THE DIGEST JOURNAL AND MAGAZINE
PREPARED BY MEKELLE UNIVERSITY LAW SCHOOL STUDENT'S



FOR MORE INFORMATION
WWW.mu.edu.et
follow us
The Digest/mu-school of law students journal and magazine
mekelle university school of law
thedigest2008@gmail.com